# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 341 ህዳር 12 2007 ገጽ 1


ታሪካዊ ገዳማት ፈርሰዋል፤ ታሪካዊ ቅርሶች ለባእዳን አልፈው ተሸጠዋል፤ የነፃነት ታሪካችን እየተደለዘ በወያኔያዊ ዘረኛ የፈጠራ ታሪክ መተካቱ ቀጥሏል፤ ታሪካዊ ጀግኖቻችንን ማዋረድና ማውገዝ የእለት ተእለት ስራቸው ሁኗል። ወያኔዎች ኢትዮጵያዊነት ቅዠት ሆኖባቸዋል፤ ስለዚህም ቀንደኛ ጠላታቸው አድርገው ፈርጀውታል። ይህ የዘረኝነትና የዘረፋ ስርዓታቸው ውሎ ማደር የሚረጋገጠው ኢትዮጵያዊነት መመታት ሲችል ብቻ ነው ብለውም በፅኑ ያምናሉ። ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊነታችንን ሊያዳክም ብሎም ሊያጠፋ ይችላል ብለው የገመቱትን ሁሉ ከመፈፀም የማይመለሱት።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## እንግሊዝ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎቿን ከየሐይማኖትና ከጎሳና የፖለቲካ ውጥረት እንዲጠነቀቁ አሳሰበች

የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ ካሉ አገሮች ጋር ስትነፃጸር የተረጋጋች ብትመስልም በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሃይማኖት፤ የጎሳና የፖለቲካ ውጥረቶች መኖራቸውን በማመልከት ውጥረቶቹ ከመቼውም ጊዜ በላይ እየተወሳሰቡና እየተባባሱ በመምጣታቸው ዜጎቿ ሊፈጠሩ ከሚችሉ ችግሮችና ግጭቶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ወይንም ጥብቅ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲወስዱ ማሳሰቡ ተዘግቧል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ለተሰማሩ የእንግሊዝ ባለሃብቶች ጭምር ባስተላለፈው መልዕክት ባለሃብቶች ከጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ሹማምንት ጋር በመሻረክ ነዋሪዎችን በማፈናቀል እየተካሄዱ ባሉት ህገወጥ የመሬት ቅርምቶች ተሳታፊ እንዳይሆኑ አበክሮ ማስጠንቀቁ ታውቋል። ከህገ ወጥ የመሬት ቅርምቱ ጋር በተያያዘ በጋምቤላ፤ በቤንሻንጉልና በሌሎችም ክልሎች አሁን ድረስ ከፍተኛ ችግሮች መኖራቸውን በመረጃው ተመልክቷል። በኢትዮጵያ ባለው ያልተረጋጋና የተቃወሰ ኢኮኖሚ ሳቢያም በአገሪቱ የተሰማሩ የእንግሊዝ ኩባንያዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሊገጥማቸው ይችላል ሲልም ከወዲሁ ጥብቅ ጥንቃቄ እንዲወስዱ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ አሳስቧል።

በተያያዘ ዜና የእንግሊዝ መንግስት ለጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ የሚሰጠው ድጎማ በአገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን በስፋት እያነጋገረ መቀጠሉ ታውቋል። የእንግሊዙ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር ኒክሌግ ሃሙስ ዕለት LBC ከተባለው የአገሪቱ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ከእንግሊዝ ግብር ከፋይ ኪስ እየተሟጠጠ ኢትዮጵያንና ህዝቧቿን ለስቃይ እየዳረገ ለሚገኘው ፋሽስታዊ አገዛዝ እንዴት ድጎማ ይሰጣል በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ኒክሌግ የጥያቄውን አግባብነት በመቀበል የእንግሊዝ መንግስት እስካሁን ድጎማ ይሰጥበት ከነበረው አካሄድ በተለየ መልኩ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩን አመላክተዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች አሜሪካ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለሚታየዉ ሰብዓዊ መብት ረገጣ ትኩረትን እንድትሰጥ ጠየቁ

አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና አክቲቪስቶቹ ወቅታዊ የኢትዮጵያን ጉዳዮችን በተመለከተ በአሜሪካ ህግ አውጭ አካል ወይንም ኮንግረሰ ስር ለሚገኘው የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ባሳለፍነው ሳምንት አጋማሽ ላይ ሰፊ ገለፃ መስጠታቸው ተዘግቧል። የኮንግረስ አባላት በተገኙበት ልዩ የምክክር መድረክ ላይ ከሂውማን ራይትስ ዎች፤ ፍሪደም ሃውስ፤ ኮሚቴ ቱ ፕሮቴክት ጆርናሊስትስ በመገኘት በኢትዮጵያ ስላለው የአፈናና የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰፊ ገለፃ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን የሰብአዊ መብት ኮሚሽኑ በወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የተነሱ አበይት ነጥቦችን በማንሳት ለሚመለከታቸው የአሜሪካ ባለስልጣናትና ህግ አውጭ አካላት ያቀርባል ተብሎ ይጠበቃል። በመድረኩ ላይ በመገኘት ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ገለፃ ያደረጉ አካላት ከመሬት ቅርምት ጋር በተገናኘ በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ክልሎች የተፈጸሙ ኢሰብአዊ ድርጊቶችን እንዲሁም የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈፀሙ ስላለው አጠቃላይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አስመልክቶ ሰፊ ሪፖርት ማቅረባቸው ታውቋል። በቅርቡ ተግባራዊ ተደርጎ የሚገኘው የፀረ ሽብር ህግ በርካታ ጋዜጠኞችን ለእስር እንዲዳረጉ ከማድረጉም በተጨማሪ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ከአገር እንዲሰደዱ ማድረጉም በምክክሩ ወቅት ተመልክቷል። በመጨረሻም አሜሪካና ሌሎችም የጉጅሌዎቹ አጋሮች በአገሪቱ ተንሰራፍቶ ያለውን የከፋ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ረገጣ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ያሳሰቡት በመድረኩ የተሳተፉ ድርጅቶች አሜሪካ የድርሻዋን መወጣት እንዳለባት አበክረው መጠየቃቸው ተዘግቧል።

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ ደቡብ ወሎ ዉስጥ ከ400 በላይ ህዝብ አፈናቅሎ መሬቱን መቸብቸቡ ተሰማ

ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ በደቡብ ወሎ ዞን በኮምቦልቻ ወረዳ ቀበሌ 11 በተለምዶ ጋሪሳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ይኖሩ የነበሩ 470 ሰዎችን ቦታ ለኢንቨስትመንት ይፈለጋል በሚል ማጭበርበሪያ ሰብአዊ መብታቸውን በመጣስ እንዲፈናቀሉ በማድረግ፣ መሬታቸው በካሬ ሜትር 1 ብር ከ 46 ሳንቲም መቸብቸቡ ተዘግቧል። በግፍ ከቦታቸው የተፈናቀሉት አርሶደአሮች አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰሚ በማጣታቸው ለስደትና ለረሃብ መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የወረዳው ጉጅሌዎች ከተፈናቃዩ ደሃ ህዝብ የወሰዱትን መሬት በሙስና መቸብቸባቸውን እርስ በርስ እየተገላለጡ ይፋ ማድረጋቸው ተመልክቷል።

የወረዳው ላይዘን ኦፊሰር ሹም ሃብቶም የተባለ ግለሰብ፣ አስተዳዳሪውን አበራ አበረን በዘረፈው የህዝብ ሃብት በአዲስ አበባና በባህርዳር መሬት ገዝቶ ቤት መስራቱን እንዲሁም ቡልዶዘሮችን ገዝቶ እያከራየ እንደሚገኝ ማጋለጡ የተመለከተ ሲሆን የወረዳዋ ምክትል ከንቲባ ደግሞ በባንክ ሂሳቡ 8 ሚሊዮን ብር እንደተገኘበትና በተለያዩ አካባቢዎች ቤቶችን መገንባቱን አጋልጠዋል። አጋላጩ ሀብቶም የተባለው ግለሰብም በራሱ በከተማዋ ሁለት ቦታ ገዝቶ ቤት መስራቱንና መቀሌ ላይ ተጨማሪ ቦታ መግዛቱን በሌሎች ባልደረቦቹ ተጋልጧል።

እነዚሁ በሙስና የነተቡት የዘራፊው ወያኔ አገዛዝ ሹማምንቶች ከዘረፋው ጋር ተያይዞ ለጊዜው ከስራቸው ቢታገዱም እስካሁን የተወሰደባቸው እርምጃ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል።

## በደቡብ ክልል በጉራፈርዳ ወረዳ ከ100 በላይ አርሶደሮች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል

አርሶ አደሮቹ የመሬት ዋስትና ወረቀት እንዲሰጣችሁ በነፍስ ወከፍ 4 ሺ 500 ብር ክፈሉ ተብለው የተጠየቁ ቢሆንም፣ እነርሱ ግን እስከዛሬ ግብር እየከፈልን ኖረናል፣ አሁን ተጨማሪ አንከፍልም በማለት መቃወማቸው ታውቋል። ይህ ተከትሎ መሬታቸውን እየተቀሙ ይዞታቸው ለኢንቨስተር በሚል ማጭበረበሪያ እየተቸበቸበ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው እየተደረገ ባለው የመሬት ቅርምት አብዛኞቹ የአገዛዙ ሹማምንቶች ተሳታፊ መሆናቸውንና ከኢንቨስተሮች ጋር አክሲዎን እንዳላቸው ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአካባቢው የሚታየው ተደጋጋሚ ግጭት ከዚሁ ጋር የተያያዘ መሆኑ በስፋት ተነግሯል።

## ከወራት በፊት በኦሮምያ ክልል ተቀስቅሶ የነበረው ደም አፋሳሽ አሁንም እንዳገረሸበት ነዉ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በኦሮምያ ክልል ከአምቦ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው ሚዳ ቀኒ አካባቢ ተማሪዎችን ወደ እስር እያጋዘ እንደሚገኝ የአፍሪካ ቀንድ የሰብአዊ መብቶች ሊግ አጋልጧል። ከወራት በፊት ጉጅሌዎቹ ከአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ ሊያደርጉት የነበረውን የመሬት ዘረፋ በተቃወሙ ተማሪዎችና ነዋሪዎች ላይ የአገዛዙ አጋዚ ጦር በወሰደው የሃይል እርምጃ ቁጥራቸው ከ 50 በላይ የሚሆኑ ሰዎች በጥይት ተደብድበው መገደላቸው ይታወሳል። የተፈጠረው ደም አፋሳሽ ግጭት በጥቂቱም ቢሆን ረገብ ያለ ቢመስልም ከባለፈው ሳምንት ጀምሮ በአዲስ መልክ ማገርሸቱንና የአገዛዙ አጋዚዎች በተማሪዎች ላይ የአፈና እርምጃ መውሰድ መጀመራቸውን ሊጉ ገልጿል። ለእስር የተዳረጉ የስምንት ሰዎችን ስም ዝርዝር ይፋ ያደረገው ሊጉ ከታሰሩት መካከል መምህራን እንደሚገኙበትም አመልክቷል። እንዲሁም በዚህ በያዝነው ወር ብቻ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ናችሁ የተባሉ ቁጥራቸው ከ 160 በላይ ሰዎች በወለጋ፤ ጅማ፤ ኤሊባቡር፤ ባሌና ቦረና ለእስር ተዳርገው እንደሚገኙ እማኞችን ዋቢ በማድረግ ሊጉ አስታውቋል። ለእስር ተዳርገው የሚገኙት ሰዎች በጉጅሌዎቹ የካንጋሮ ፍርድ ቤት የሃሰት ምስክርነት እየተሰጠባቸው ለከፋ የረጅም ጊዜ እስር እየተዳረጉ እንደሚገኙም ድርጅቱ አስታውቋል። በተለይ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች እስራቱ ቀጥሎ እንደሚገኝ ያስታወቀው ሊጉ የተቃዋሚ ሃይሎች ካላቸው የአቅም ውስንነትና በጉጅሌዎቹ እየደረሰባቸው ባለው ወከባና ጫና የተነሳ በአገዛዙ እየታሰሩ፤ እየታፈኑና እየተገደሉ የሚገኙ ሰዎችን እየተከታተሉ ይፋ ማድረግ አለመቻላቸው ተመልክቷል። በቅርቡ መቀመጫውን በእንግሊዝ ያደረገው አምንስቲ ኢንተርናሽናል ባለፉት 3 አመታት ብቻ ከ 5000 የሚልቁ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ለእስር ተዳርገው እንደሚገኙ መግለጹ አይዘነጋም። የተቃዋሚ ሃይሎች በበኩላቸው የታሳሪዎቹ ቁጥር ከ 22 ሺህ እንደሚልቅ መግለፃቸው ይታወሳል።

## መምጫውን የማያውቅ መድረሻውን ያጣል

ታሪክ ለሰው ልጅ ስሩና መሠረቱ ነው። ታሪኩንና መምጫውን የማያውቅ ህዝብ መድርሻውን የማያውቅና ራሱንም ለባርነት አሳልፎ የሰጠ ይሆናል። ለክብሩ ለእርሱነቱ ለህብረቱና ለነፃነቱ ፀንቶ መቆየት እና የጥንካሬውና ተሳስሮ የመዝለቂያው ሰንሰለት ታሪኩ መሆኑ ይታወቃል።

የአሜሪካ ባርያ ፈንጋዮች ትናንት በገፍ ከአፍሪካ በባርነት ያመጡዋቸው አፍሪካውያን አንድ ቀን በአንድ ቆመውና በህብረታቸው ጠንክረው ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት እንዳይነሱ ሀ ብለው የነጠቋቸው ማንነታቸውን፤ ታሪካቸውንና መገኛቸውን ነበር። እንደ እቅዳቸውም እነሆ ዛሬ አብዛኛው ጥቁር አሜሪካዊ እኔ ማን ነኝ? መምጫዬስ ከወደየት ነው? በሚሉና በመሳሰሉ ጥያቄዎች ተተብትቦ ለምላሹ ሲውተረተር መገኘቱ፤ እንዲሁም ዛሬም ከተገዢነት መንፈስ ራሱን አላቆ በሁለት እግሩ ለመቆም ሲታትር ይገኛል።

ሌላው የኢጣልያ ወራሪን ሀይል ቅስም የሰበረውና በአለም አቀፍ ደረጃ ቅሌት ያከናነበው የአድዋ ጦርነት መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ቅሌት በደም አጥቦ ሀያልነቱን ለአለም ለማሳየት በሞከረበት ሁለተኛው ወረራ ወቅት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የአድዋ ጦርነት የመሩት የአፄ ሚንሊክ ሀውልትን ከጥልቅ ጉድጓድ መቅበር እንደነበር አይዘነጋም። ባጠቃላይ አንድ ህዝብ እንደ ህዝብና ሀገር ጠንክሮና በነፃነት ኮርቶ ለመኖር ብሎም ከትውልድ ትውልድ መሸጋገር መቻል ከማረጋገጫው  አንዱ የትናንት ማንነቱና የመገኛ ታሪኩ መሆኑን ከላይ በምሳሌነት ያነሳናቸው ነጥቦች ያረጋግጣሉ።

ታሪክ ለአንድ ህዝብ የማንነቱ መገኛ፤ የመገኛው ምንጩና መምጫውን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የነገ መዳረሻውን የመመልከቻ መነፅርና ጠንክሮ የመንቀሳቀሻው ጉልበቱ ሆኖ የሚያገለግል ትልቅ መሳሪያ ነው። ይህ ማለት ደግሞ አንድ ህዝብ ታሪኩ ከጠፋ ሊገጥመው የሚችለው ችግርና ፈተና እንዲህ በቀላሉ የሚገመት ያለመሆኑንና እንደ ህዝብ እንደ ሀገር ቀጣይነቱን በቀላሉ መፍትሄ ከማይገኝለት ፈተና ውስጥ ይከተዋል ማለት ነው።

ኢትዮጵያችን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ ህልውናዋ አደጋ ላይ የወደቀበት መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም፡ባለፉት 23 አመታት በዘረኞቹ የወያኔ ጉጅሌዎች እጅ ከወደቀችበት እለት ጀምሮ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መገለጫ የሆኑ የታሪካችንና የባህልችን ዋና ዋና እሴቶች ዋነኛ ኢላማ ሆነዋል። ይህንንም በተደጋጋሚና በግልፅ ከወያኔው መሪ እስከ ተራ ደጋፊው የሚወረወረው በትር ያረጋግጣል። ጉጅሌዎቹ የነፃነት ምልክት የሆነውንና በዕልፍ አዕላፋት ደም መሥዋዕትነት ፀንቶ የቆየውን ሰንደቅ ዓላማ በሶ መጠቅለያ ጨርቅ ከማድረግ ጀምረው ዛሬ በምሁራን ጥረትና በእያንዳንዱ ዜጋ ድጋፍ የተሰባሰቡት የታሪኮቻችን መዛግብት በጥንቃቄ ከተቀመጡበት (ቤተ-መዛግብት) እያወጡ ከማውደምና ለስኳር መጠቅለያነት እስከ መሸጥ ደርሰዋል።

ታሪካዊ ገዳማት ፈርሰዋል፤ ታሪካዊ ቅርሶች ለባእዳን አልፈው ተሸጠዋል፤ የነፃነት ታሪካችን እየተደለዘ በወያኔያዊ ዘረኛ የፈጠራ ታሪክ መተካቱ ቀጥሏል፤ ታሪካዊ ጀግኖቻችንን ማዋረድና ማውገዝ የእለት ተእለት ስራቸው ሁኗል። ወያኔዎች ኢትዮጵያዊነት ቅዠት ሆኖባቸዋል፤ ስለዚህም ቀንደኛ ጠላታቸው አድርገው ፈርጀውታል። ይህ የዘረኝነትና የዘረፋ ስርዓታቸው ውሎ ማደር የሚረጋገጠው ኢትዮጵያዊነት መመታት ሲችል ብቻ ነው ብለውም በፅኑ ያምናሉ። ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊነታችንን ሊያዳክም ብሎም ሊያጠፋ ይችላል ብለው የገመቱትን ሁሉ ከመፈፀም የማይመለሱት። ለዚህም ነው በስንት ጥረትና በብዙዎች ድካም ተሰባስቦና ተደራጅቶ የቆየውን የታሪክ መዛግብትና መፅሀፍት ከቤተ-መዘክር አውጥቶ በኪሎ ለመቸብቸብ የበቁት።

ታዲያ ኢትዮጵዊ ነን የምንል ሁሉ ዘሬም እንደትናንቱ ይህን በማንነታችን ላይ የሚደረግ የጥፋት ዘመቻ ለማስቆም መነሳት ግድ ይለናል። እየተፈፀመ ያለው የታሪክ ማጥፋት ዘመቻ ለነፃነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ከምናደርገው ትግል እኩል ጎን ለጎን ለታሪካዊ ቅርሶቻችንና መዛግብቶቻችን ከጥፋት የመከላከልና የማዳን ስራ የመስራት የትውልድ ኃላፊነት አለብን። አለበለዚያ መምጫውን የማያውቅ መድረሻውን አያውቅምና የምናደርገው የነፃነት ትግል የተሟላ ውጤት ማስገኘቱ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ተገንዝበንም ወያኔን በቃህ ልንለው ይገባል።

በመጨረሻም ጂኦርጅ ኦርዌል *'The most effective way to destroy people is to deny and obliterate their understanding of their own history"* ብሎ ጽፎ ነበር ።ህወሃቶች የዚህ ፍልስፍና ተከታዮች መሆንን በመምረጥ ለራሳቸው ውረደትን፤ ለአገራቸውም ውደቀትን ተመኝተዋል። ኢትዮጵያችን መንግስት በጠላትነት ተሰልፎ ከአገራችን ከህዝብና ለአገሪቷ እሴቶች ጋር የሚዋጋበት አገር ሁናለች። ህወሃት በብዙ መልኩ ሲታይ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት መሆንን የመረጠ ቡድን ነው።የህወሃት በኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት መቆሙ ያስቆጣቸው ወጣቶች እምቢ ለአገሬ፤ እምቢ ለክብሬ ብለው ተነስተው ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ተሠማርተዋል። ግዜው ከእነዚህ ወጣቶች ጎን የምንቆምበትም ጭምር ነውና ተነሱና ለነፃነታችንና ለአገራችን ዝና ለህዝባችን ክብር አብረን  ታግለን ጠላትን የመረጠውን ህወሃትን እናስወግድ እና ንፁህ አገር እንፍጠር።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

---

## የጅማ ህዝብ በወያኔ መማረሩን ገለጸ

የኦሮምያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሙክታር ከድር፣ የገንዝብ ሚኒስትሩ ሶፍያን አህመድና የኦሮምያ የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊው ከጅማ ዞን የተውጣጡ የተለያዩ ድርጅት ተወካዮችን በጊዜ አዳራሽ ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት፣ ህዝቡ በአስተዳደሩ ተስፋ መቁረጡንና ለውጥ የሚፈልግ መሆኑን ተናግሯል። የምርጫ ቅስቀሳ በሚመስለው መድረክ፣ አቶ ሙክታር ተሰብሳቢው የሚሰማውን እንዲናገር ፈቅደዋል። ነዋሪዎቹ በዞኑ ልማት የሚባል ነገር እንደሌለ፣ ከጅማ አጋሮ የተሰራው የአስፋል መንገድ ፈራርሶ ህዝቡ ከመቸገሩም በላይ በተለይም ወላዶች ወደ ጅማ ሆስፒታል በሚሄዱበት ጊዜ መንገድ ላይ እንደሚሞቱ ተግልጿል።

በከተማው የሚገኙ ወታደሮች ነዋሪውን እየገደሉና እያሰቃዩ መሆኑን በቅርቡ የተፈጸሙ አሰቃቂ ግድያዎችን በማንሳት አቤቱታዎችን አሰምተዋል። በዞኑ የተስፋፋው ሙስና ከአቅማችን በላይ ሆኗል ያሉት ነዋሪዎች ባለስልጣኖች የሚሾሙት ግንዘብ ዘርፈው ፎቅ ለመስራት ወይም ድርጅት ለመክፈት ነው በማለት የመንግስት ባለስልጣናት በከተማው ውስጥ የሚቀሙዋቸውን ቤቶችና ቦታዎችን በዝርዝር በመግለጽ አቅርበዋል። የህዝቡ ቁጣ ያስደነገጣቸው አቶ ሙክታር ከድር ከስብሰባው በሁዋላ የተለያዩ ባለስልጣኖችን ሴንትራል ሆቴል በመሰብሰብ፣ የህዝቡ ብሶት ከልክ ማለፉን እንደገለጹና አፋጣኝ እርምጃ ተወስዶ የማረጋጋት ስራ እንዲሰራ አዘዋል።
በቅርቡ በአካባቢው የሰፈሩ ወታደሮች አንድ ወጣት እስከ አያቱ በሌሊት በጥይት ደብድበው መግለደላቸው መዘገቡ ይታወሳል። አርቲስ ወንዴ የተባለ ድምጻዊም እንዲሁ በወታደሮች ተደብድቦ ሆስፒታል ተኝቶ ሲታከም ከቆየ በሁዋላ፣ በአሁኑ ጊዜ በውጭ ሆኖ በማገገም ላይ ይገኛል። ዘጋቢያችን ያነጋገረው አርቲስት እርሱና ልጁ በከፍተኛ ሁኔታ መደብደባቸውን በመግለጽ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ያመራ በመሆኑ፣ ከፍርድ ውሳኔ በፊት ለመናገር እንደሚከብደው ገልጿል። በተመሳሳይ መልኩም በሃረር የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ በሚል አጀንዳ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ህዝቡ ተቃውሞውን አሰምቷል። መድረኩን የመሩት የክልሉ ፕሬዚዳንት እና ምክትላቸው ሲሆኑ፣ ፕሬዚዳንቱ በያዝነው አመት ያጋጠሙ የመልካም አስተዳድር ችግሮችን ህዝቡ እንዲናገር በፈቀዱት መሰረት ተሰብሳቢው እድሉን በመጠቀም ብሶቱን አሰምቷል። አንዳንድ ነዋሪዎች ” ልጆቻችን ስራ አጥ ሆነዋል፣ እዚህ አካባቢ ከ60 አመታት በላይ ብንኖርም አሁን ግን ስራ እንዳናገኝ ታግደናል፣ የት ሂዱ ነው የምትሉን?” በማለት በአካባቢው የሚታየው ዘረኝነት እንዳስመረራቸው ገልጸዋል። ባድሜ ዘምተው በመቁሰላቸው በቦርድ የተሰናበቱ ወታደሮች ደግሞ መስተዳድሩ እውቅና እንደነፈጋቸውና መብቶቻቸው እንዳልተከበሩላቸው ተናግረዋል።በከተማዋ ውስጥ ፍትሃዊ የልማት ስርጭት አለመኖሩን የገለጹት ነዋሪዎች፣ በተለይ መጤዎች በሚባሉት አካባቢዎች ምንም አይነት የመሰረተልማት አገልግሎት እንዳልተዘረጋላቸው በምሬት ገልጸዋል። ህዝቡ በርካታ ጥያቄዎችን ቢያነሳም ፕሬዚዳንቱ ጥያቄዎችን በወረዳ ደረጃ ታገናላችሁ በማለታቸው ህዝቡ አዳራሹን እየለቀቀ ወጥቷል።

# ታሪክን ማደብዝዝም ማጥፋትም አይቻልም!

በአለማችን በተለይ አፍሪካ ዉስጥ የአገርን ብሄራዊ ኃብት የሚዘርፉ፤ የህዝብን መብት የሚረግጡና አገርን እነሱ ባሰኛቸዉ አቅጣጫ ብቻ ይዘዉ የሚነጉዱ አያሌ ፈላጭ ቆራጭ መንግስታት አሉ። እነዚህ ህዝብን የሚበድሉ መንግስታት ሁሉም በጥቅሉ አምባገነን ይባሉ እንጂ በመካከላቸዉ ጎላ ብሎ የሚታይ ትልቅ ልዩነት አለ። ሆኖም የቱንም ያክል ልዩነት ቢኖርም እንደ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች እንመራዋለን የሚሉትን ህዝብ የሚንቁና የኛ ነዉ የሚሉትን አገር የሚጠሉ አምባገነን መንግስታት የሉም፤ በታሪክም ኖረዉ አያዉቁም። አምባገነን መንግስታት የስልጣን ዘመናቸዉን ለማራዘምና ከስልጣን ጋር ተያይዞ የሚመጣዉን ክብር፤ ዝናና ጥቅማ ጥቅም እንዳይቋረጥ ሲሉ የሚቃወማቸዉንና ለስልጣን ዘመናቸዉ አደጋ ነዉ የሚሉትን ሁሉ ያስራሉ፤ ይደበድባሉ ወይም ይገድላሉ። እነዚህን ነገሮች የወያኔ መሪዎችም ያደርጋሉ፤ ነገር ግን በወያኔና በሌሎቹ አምባገነን አገዛዞች መካከል እጅግ በጣም ትልቅ ልዩነት አለ። ለምሳሌ ወያኔዎች ዘረኛ አምባገነኖች ናቸዉ፤ የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን እንደ ጥገት ላም አንጂ እንደ አገራቸዉ አይመለከቱም። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያን፤ ህዝቧንና ታሪኳን ይንቃሉ፤ ያንኳስሳሉ።

ባለፉት አምስትና ስድስት አመታት በግልጽ እንደተመለከትነዉ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ገበሬ ከመሬቱ አፋናቅለዉ ለምለም መሬቱን ለባዕዳንና ለህወሓት የጦር መኮንኖች ሰጥተዋል። መሬቴንና ቤቴን አልለቅም ብሎ የተቀናቀናቸዉን ደግሞ በጅምላ ገድለዋል። በከተሞች ዉስጥም ከተሜዉን ምንም ካሳ ሳይከፍሉት ዕድሜ ልኩን ከኖረበት ቤቱ እያፈናቀሉ ከነቤተሰቡ ሜዳ ላይ ጥለዉት መሬቱን ባለኃብት ለሚሏቸዉ የወያኔ ባለሚሎች ሰጥተዋል። በአጠቃላይ የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያ አንድነት፤ በታሪኳና በህዝቧ ላይ እንዲህ ነዉ ተብሎ ለመናገር የሚዳግት ትልቅ በደል ፈጽመዋል። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በእናት አገራችን ላይ ያደረሱት በደል ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለምና ዛሬ ወደዚያ ዝርዝር ዉስጥ አንገባም፤ ዛሬ ትኩረት የምንሰጠዉ ወያኔ ደግሞ ደጋግሞ ከዘመተባቸዉና ሙሉ ኃይሉን ካሳረፈባቸዉ የአገራችን እሴቶች አንዱ ታሪካችን ነዉና የዛሬዉ ቆይታችን በዚሁ በታሪካችን አካባቢ ይሆናል።

ታሪክ በአንድ አገር ዉስጥ እያንዳንዱ ትዉልድ ከሱ የቀደመዉ ትዉልድ በግል፤ በቡድንና በማህበረሰብ ደረጃ የተጓዘበትን መንገድ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ካለፈዉ የምንማርበትና የወደፊቱን ጉዟችንን ለመጀመር በመረጃነት የሚያገለግለንን እዉቀት የምናገኝበት የጥበብ ድርሳን ነዉ። የማንም አገር ታሪክ ዉብ ሆኖ የሚያምርና የማያምር ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ የማያምረንን የታሪክ ጠባሳ ወደ ኋላ ሄደን ማከም በፍጹም እንደማንችል ሁሉ የወደፊቱን ታሪካችንንም የብዙ ማህበረሰባዊ መስተጋብሮች ዉጤት ነዉና ያሰኘንን ቅርጽና ይዘት ልንሰጠዉ አንችልም። የታሪክ ዋናዉና ትልቁ ቁም ነገር የታሪኩ ባለቤት የሆነዉ ማህብረሰብ እራሱን ወደ ኋላም ወደ ፊትም የሚመለትበት መስኮት መሆኑ ነዉ። ምንም አይነት ታሪክ የሌለዉ ህብረተሰብ የለም፤ ካለም ከየት አንደመጣና ወዴት አንደሚሄድም አያዉቅም።

አገራችን ኢትዮጵያ ረጂምና ጥንታዊ ታሪክ ካላቸዉ ጥቂት አገሮች ዉስጥ አንዷ ናት። ይህ ረጂም ታሪካችን ደግሞ አንገት ቀና የሚያስደርግ የድልና የገድል ታሪክ አንደሆነ ሁሉ አንገት የሚያስደፋ የግፍና የበደል ታሪክም አለበት። የዛሬዉ ትዉልድ ኢትዮጵያዊ ካለፈዉ ታሪኩ ከበደሉም ከገድሉም ተምሮ የወደፊት አካሄዱን ከሞላጎደል መቆጣጠር የሚችል እድለኛ ትዉልድ ነዉና አባቶቹ ባቆዩለት ታሪክ ሊኮራ ይገባል። አንድ ህዝብ በታሪኩ እንዲኮራ ደግሞ ታሪኩ በተደጋጋሚ ሊነገረዉ ሊተረክለትና በጽሁም መልክትም በገፍ ሊቀርብለት ይገባል። የአገራችን የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ለዚህ የታደለ አይደለም ፤ ምክንያቱም እንመራሀለን የሚሉት መሪዎቹ ታሪኩን የሚያንቋሽሹና የሚንቁ መሪዎች ናቸዉ።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ካደረሱትና ዛሬም በማድረስ ላይ ካሉት በደሎች አንዱና ዋነኛዉ የኢትዮጲያን ታሪክ ለባዕዳንና የታሪኩ ባለቤት ለሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አሳንሰዉና እንደ ተራ ዕቃ አቃልለዉ ማቅረባቸዉ ነዉ። የወያኔ መሪዎች አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ መጀመሪያ ከተናገሯቸዉ ንግግሮች አንዱ የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪክ የመቶ አመት ታሪክ ነዉ ያሉት አስቀያሚ ንግግር ነዉ። በዚህ አባባል ላይ የጸና አቋም ካላቸዉ የወያኔ መሪዎች ዉስጥ ዛሬ በህይወት የማይገኘዉ መለስ ዜናዊና ጓደኛዉ ስብሐት ነጋ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። የሚገርመዉ እነዚህ የኢትዮጵያን ታሪክ በአንድ መቶ አመት የወሰኑት ሁለት ግለሰቦች የተወለዱት የኢትዮጵያ ህዝብ የዛሬ 119 አመት በአፄ ሚኒልክ መሪነት ወራሪዉን የጣሊያን ጦር አይቀጡ ቅጣት በቀጡበት አድዋ ዉስጥ ነዉ።

ወያኔ ካለፈዉ መስከረም ወር ጀምሮ ባደበዘዘዉ ቁጥር እያሽበረቀ ያስቸገረዉን የኢትዮጵያ ታሪክ ለማቆሸሸ ጠባሳዉ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ የክፋት ስራ እየሰራ ነዉ። ኢትዮጵያን የመሰለ ባለታሪክ አገር ገድሎ ለሞተዉ ዘረኛ ሰዉ ትልቅ ማዕከል በህዝብ ገንዘብ የሚያሰሩት የወያኔ መሪዎች ማስቀመጫ ቦታ ጠፋ እያሉ አያሌ ብርቅ የሆኑ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሀፍትን ከወመዘክር አይወጡ በችርቻሮ እየሸጡ ነዉ። እነዚህ ወያኔ የሚሸጣቸዉ መጽሐፍት የተጻፉት በተለያዩ ዘመናት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዉ በነበሩት የእንግሊዝ፤ የፈረንሳይ፤ የጣሊያን፤ የስፔንና የጀርመን የታሪክ ጸሐፊዎች ነዉ። ከሰሞኑ ከአዲስ አበባ የሚመጡ ዜናዎች እንደሚያመለክቱት ወያኔ በዉጭ አገር የታሪክ ጸሐፊዎች የተጻፉትን የታሪክ መጽሐፍትና ተጠረዝዉ የተቀመጡ ቆየት ያሉ ጋዜጣዎችን በርካሽ ዋጋ እየቸበቸቡ የግሮሰሪ ዕቃ መጠቅለያ አድርጓቸዋል።

ይህንን አሳፋሪ የሆነ የወያኔ የመጽሐፍ ሽያጭ እንደ ተራ ወንጀል የምናልፍ ኢትዮጵያዉያን ካለን እጅግ በጣም ተሳስተናል። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የሚሰሩትን ስራ አበክረዉ የሚያዉቁ ሰዎች ናቸዉ፤ እያሰሩ ያሉት ስራ ደግሞ ግልጽ ነዉ። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የተጻፈ ታሪካችንን ብቻ ሳይሆን እያወደሙ ያሉት ባህላችንን፤ ወጋችንንና ቅርሶቻችንን ጨምር ነዉ እንዳልነበረ ያደረጉት። ለምሳሌ በብዙ የአለም አገሮች ዉስጥ ረጂም ዕድሜ ያስቆጠሩ ህንፃዎች፤ የታሪካዊ ሰዎች መኖሪያ ቤቶችና የተለያዩ የአገር ቅርሳቅርሶች ልዩ እንክብካቤ እየተደረገላቸዉ ከዘመን ወደ ዘመን እንዲተላለፉ የደረጋል። ኢትዮጵያ ወስጥ ግን ዕድሜ ለወያኔ ከፍተና ታሪካዊ እሴት ያላቸዉ ህንፃዎች በልማት ስም እንዲፈርሱ ይደረጋል። የጀግኖችን አጽም ያረፈበት የመቃብር ቦታም በግሬደር እየተደረመሰ የንግድና የችርቻሮ ቦታ ይሆናል።

ሌለዉ ወያኔ በታሪካችን ላይ የሚያደርሰዉ ጥፋት ታሪካችንን እንዳንማርና የታሪክ ተማራማሪዎቻችን በጥንታዊ ታሪካችን ላይ ምርምር እንዳያደርጉ እጅና እግራቸዉን ማሰሩ ነዉ። ለምሳሌ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የሚገኘዉ የታሪክ ዲፓርትመንት የኢትዮጵያን ታሪክ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ታሪካችንን ከተለያየ አቅጣጫ በማጥናትና ምርምር በማድረግ ለታሪካችን መበልጸግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ተቋም ነዉ። ሆኖም ይህ በተለያዩ መንግስታት ዉስጥ ለረጂም አመታት ትልቅ ስራ ሲሰራ የቆየዉ የታሪክ ዲፓርትመንት ዛሬ አለ ተብሎ መናገር በማይቻልበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ወያኔ የቀድሞ ታሪካችንን እያወደመ የሚቀጥለዉን ታሪካችንን ደግሞ በራሱ አቅጣጫ እያጣመመ በመጻፍ ላይ መሆኑን ነዉ።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ታሪክ አስመልክቶ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፈዉ በተወሰኑ ሰዎች ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ነዉ ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ የረጂሙን ዘመን የአገራችን የኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ ሞቶ አመታ የበለጠ ዕድሜ የለዉም እያሉ በተደጋጋሚ ተናግረዋል። ዛሬ በገፍ ለጨረታ ያቀረቧቸዉ የታሪክ መጽሐፍት ቁልጭ አድርገዉ የሚናገሩት ደግሞ ታሪካችን ከ3000 ሺ አመታት በላይ መሆኑንና የተጻፈዉም በተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ኢትዮጵያዉያንና የዉጭ አገር ሰዎች ጭምር መሆኑንደ ነዉ። ዛሬ ወያኔ እንደ ርካሽ ዕቃ እያወጣ የሚቸበችባቸዉ መጽሀፍት ለዚህ አሳዛኝ ዕጣ የበቁት ይህንን የወያኔ አይን ያወጣ ዉሸት ስለሚያጋልጡ ነዉ።

አገራችን ኢትዮጵያን እንወዳለን የምንል ኢትዮጵያዉያን በሙሉ ይህ በአፋችን ሁሌም የምንለዉ ቃል በተግባር የምንተረጉምበት አጋጣሚ ፊት ለፊታችን ላይ ተደቅኗል። ኢትዮጵያ አንደ ገና ዳቦ ከላይና ከታች ወያኔ ባነደደዉ ረመጥ እሳት እየተለበለበች ነዉ። ይህንን እሳት ማጥፍትና አገራችንን ከወያኔ መታደግ ካለብን ግዜዉ ነገ ሳይሆን ዛሬ ነዉ።

አያሌ ኢትዮጵያዉያን የወያኔን የመጽሐፍ ሽያጭ አስመልክቶ የወሰዱትን ቆራጥና ብልህ እርምጃ ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና፤ የዲሞክራሲ ንቅናቄ እጅግ በጣም ያደንቃል። በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የሚገኙ አያሌ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን የአገርና የወገን ሃላፊነት ተሰምቷቸዉ ወያኔ ለጨረታ ያቀረበዉን መጽሐፍ በመግዛት የአገራቸዉን ታሪክ ለመታደግ ያደረጉት ጥረት በዋጋ ሊተመን የማይችል ትልቅ አገራዊ ስራ ነዉ። አገራችን ዛሬ ባለችበት ሁኔታ ነገ አትገኝም የሚል እምነታችን የጸና ነዉና እነዚህን የገዛችኋቸዉን መጽሀፍት በጥንቃቄ በመያዝ ሀላፊነትና የአገር አደራ ለሚሰማዉ በህዝብ የተመረጠ መንግስት አንድታስረክቡ አደራ እንላችኋለን። ከአሁን በኋላም ቢሆን የወያኔን ፀረ አገርና ፀረ ህዝብ ስራ እየተከታተላችሁ እንድታከሽፉና በሚያልፈዉ ህይወታችሁ የማያልፍ ታሪክ ሰርታችሁ ወያኔን በማሰወገዱ ዘመቻ ዉስጥ ሙሉ ተሳትፎ አንድታደርጉ አገራዊ ጥሪ እናስተላለፋለን።

## ሰንደቅ ዓላማችን ላይ የተለጠፈዉ ባዕድ አካል ይነሳ የሚለዉ ጥያቄ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ነዉ

በቅርቡ አገር ዉስጥ በሚታተመዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ “የሰንደቅ ዓላማ ቀን ክብረ በዓል በብሔራዊ ቀን ቢታጀብስ” በሚል ርዕስ አንድ ጽሁፍ ቀርቦ ነበር። ጸሐፊዉ ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ.ም. የተከበረው ሰባተኛው ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን “ቀትረ ቀላል” ነዉ የሚል የራሳቸዉን አስተያየት ሰጥተዉ እንደነበር ይታወሳል። እንደ ጸሐፊዉ አባባል ይህንን ለማለት የበቁት ከብሔራዊው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በላይ የክልል ሰንደቅ ዓላማዎች ነግሰው በመታየታቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

ከሰሞኑ ደግሞ እዚያዉ ሪፖርተር ላይ አቶ አያሌዉ አስረስ የተባዩ ግለሰብ ሰንደቅ አላማችንን በተመለከተ ሌላ ድንቅ የሆነ ጽሁፍ አስነብበዉናል። በእኔ እምነት ይላሉ አቶ አያሌዉ “የሰንደቅ ዓላማዉን ቀን ቀትረ ቀላል ያደረገው አገራችን ዉስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር እየሰደደ የመጣው ብሔርተኝነት ነው”። ወያኔ ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀንን እንዲያውጅ የገፋፋትን ነገሮች ስንመለከት በዓሉ ከድርጅት አጀንዳነት እንዳይወጣና የመንግሥት ወዳጆችም ሆነ ተቀናቃኞች ባንድነት እንዳያከብሩት ያደረገበትን ምክንያት ለመረዳት ያግዘናል። ወያኔ በዓሉን ያወጀው በሕዝቦች መካከል ብሔራዊ አንድነትን የማነጽ ግብ ይዞ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ዓላማ ፍፁም ትክክል ነው ብለን ብናስብ እንኳን ችግሩ ወያኔ ጠዋት ስለተባበረችና አንድ ስለሆነች አገር ይናገርና ከሰዓት በኋላ ስለ መለያየትና ስለመገነጣጠል ነዉ የሚሰብከው።

ሕወሓትና ኢሕዴን (አሁን ብአዴን) በጦር ሜዳ በቆዩባቸው በርካታ ዓመታት ዓርማም ሰንደቅ ዓላማም አድርገው ሲገለገሉበት የኖሩት የየራሳቸው ድርጅታዊ መለያ ነበራቸው (ይህ መለያ ዛሬ የየክልላቸው መንግሥታት ባንዲራ ሆኗል)። በየድርጅቶቻቸው ስብሰባ ላይና በፕሮግራሞቻቸው ወቅት የተቀረፁ የቪዲዮ ምስሎች የሚመሰክሩት ይህንኑ ነው። ይህ ደግሞ ለብሔራዊው ሰንደቅ ዓላማ ቦታ እንዳልነበራቸውና አሁንም እንደሌላቸዉ ያመለክታል። በውጊያ ወቅት በእጃቸው ለሚገባው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የነበራቸው አያያዝም የስኳርና የጨው መቋጠሪያ እስከ ማድረግ ድረስ እጅግ ክብረ ነክ እንደነበረ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት የተማረኩ አባሎቻቸው ገልጸዋል። ደርግ ይህን ለፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታ ማዋሉም አይዘነጋም። በኋላም አዲስ አበባን በተቆጣጠሩ ማግስት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሰንደቅ ዓላማ ጨርቅ ነው በማለት የተናገረዉ እሱም ሆነ የሚመራዉ መንግሥት ለሰንደቅ ዓላማው አክብሮት እንደሌላቸው እንደ ማረጋገጫ ተቆጠረ። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ኢሕአዴግንና መንግሥቱን እንደ ቆላ ቁስል ውስጥ ውስጡን ሲበሉት ቆዩ።

በ1997 ዓ.ም. በተካሄደው ሦስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ከቀደሙት ምርጫዎች በላቀ መጠን መንግሥት ተቀናቃኝ ኃይሎች ሰፊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አየር ሰዓት እንዲያገኙ ፈቀደ። ተቀናቃኝ ኃይሎች፣ ኢሕአዴግ በያዘው የፖለቲካ አቋም የተነሳ ኢትዮጵያን የባህር በር ማሳጣቱን፣ በብሔር ላይ የተመሠረተ የፌዴራል አስተዳደር ዘርግቶ ብሔርን ከብሔር እያቃቃረ መሆኑን፣ ለብሔራዊው ሰንደቅ ዓላማ አክብሮት እንደሌለው ወዘተ… በመዘርዘር በቴሌቪዥን መስኮት ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ኢሕአዴግንና የሚመራውን መንግሥት ቁም ስቅላቸውን አሳዩዋቸው። በዚያ ምርጫ ለደረሰበት ሽንፈት የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ያበረከተውን ድርሻ የተገነዘበው ኢሕአዴግ ስለ ሰንደቅ ዓላማ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት አመነ። ‘እኔም የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር አለኝ’ ለማለት በየዓመቱ ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን እንዲከበር አወጀ። የአዋጁ ዓላማና እየተከበረበት ያለው መንፈስ ግን የሚገናኙ አልሆኑም። ወ/ሮ ሒሩትም የታዘቡት ይህንኑ ነው።

አበው ርጥብ ሬሳ ደረቅ ያስነሳ ይላሉ። አቶ በሪሁን ተሻለ የተባሉ ጸሐፊ “የሰንደቅ ዓላማ ቀን የሕዝብ በዓል ነው ወይ?” እና “ዓርማ የሌለው ሰንደቅ ዓላማ ነውሩ ምንድን ነው?” በሚሉ ርዕሶች ሐምሌ 13 እና 26 ቀን 2006 በወጡት የሪፖርተር ዕትሞች ላይ ጽፈው እንዳስነበቡን ይታወሳል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት “የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ላይ ለምን ተዘመተ?” በሚል ርዕስ ለእሳቸው በሰጠው መልስም ጉዳዩ አነጋጋሪነቱን እንደያዘ መቆየቱን የሪፖርተር አንባቢዎች እንደሚያስታውሱ አምናለሁ። ጊዜው ቢዘገይም አጀንዳው የሚያረጅና የሚሞት ባለመሆኑ ዛሬ መልሼ ልቀሰቅሰው ተገድጃለሁ።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 3.1 “የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀል ቢጫ ከታች ቀይ ሆኖ በመሀሉ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው አግድም ይቀመጣሉ፤” ይላል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ደግሞ “ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ፣ የኢትዮጵያን ብሔሮች ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል” ተብሎ ተደንግጓል። መንግሥታት በየዘመናቸው መገለጫችን የሚሉትን ዓርማ ስለሚያወጡ ኢሕአዴግ እንዲህ መደንገጉ የተለመደ አሠራር በመሆኑ የሚያስወቅሰው አይደለም።

ወቀሳና ተቃውሞ የሚቀሰቀሰው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፣ በሰማያዊ መደብ ላይ ባለ አምስት ጨረርና ባለ አምስት ጫፍ ኮከቡን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ዓርማ እስካልያዘ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 654/2001 በአንቀጽ 16 መደንገጉ ነው። ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀና በሥራ ላይ ከዋለ ከ14 ዓመታት በኋላ የወጣው ይህ አዋጅ እስከዚያ ጊዜ ድረስ በሥራ ላይ የቆየውንና በሕዝብ እጅ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ክብረ ቢስና ተራ ጨርቅ ያደርገዋል። የአቶ ዘሪሁን ተሻለም ሆነ የእኔ ተቃውሞ የሚመነጨው ከዚህ ነው። ተቃውሟችን ፌዴራል መንግሥቱ ለምን ዓርማ ይኖረዋል ሳይሆን ዓርማ የሌለው ሰንደቅ ዓላማ መጠቀም ለምን ሕገ ወጥ ይሆናል ነው።

ተወደደም ተጠላ ከነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ወዲህ ያለውና ሕጋዊው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ባለአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይና ሰማያዊ ቀለም ነው። “ባንዲራችን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ…” በማለት መዘመር ቀርቷል። ከሕዝብ እምነትና ፍላጐት ውጪ ሰንደቅ ዓላማችን ተለውጧል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በደስታውም በመከራውም ጊዜ ሰንደቅ ዓላማን የሚጠቀም ሕዝብ ነው። በትግራይ አንድ ሰው ሲሞት አካባቢው ለሟች ያለውን አክብሮት የሚገልጸው ሰንደቅ ዓላማ ይዞ በመውጣት ነው። የሚጠየቀው ስንት ሠንጋ ታረደ ተብሎ ሳይሆን፣ ስንት ሰንደቅ ዓላማ ወጣለት ተብሎ ነው። በገጠርም ሆነ በከተማ አዳራሾች የሚደምቁት በባንዲራ ነው። እናቶች አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ዶቃዎችን በልጆቻቸው ፀጉር ላይ በማስገባት ወይም የአንገት ጌጥ በማድረግ ለልጆቻቸው ስለሰንደቅ ዓላማና ስለአገር ፍቅር ለማስተማር የነበራቸውን ዕድል አዋጁ እንዲያጡት አድርጓል፤ ለምን ቢባል አሁን ሰማያዊ ቀለም የተጨመረ ሲሆን ባለ ሰማያዊ ቀለም ዶቃ ደግሞ ከተቀሩት ቀለማት ጋር አብሮ ቢደረደር ሰንደቅ ዓላማውን በትክክል አያስገኝም። ሰማያዊው ቀለም ባመጣው በዚህ ጦስ የተነሳ አባቶች የነጠላቸውንና የጋቢያቸውን፣ እናቶች ደግሞ የኩታቸውንና የቀሚሳቸውን ጥለት አረንጓዴ ቢጫና ቀይ በማድረግ በአገራቸው ሰንደቅ ዓላማ የመዋባቸው ዕድል እንደ ጉም ተኖ ጠፍቷል። ዛሬ በየከተማው በወጣቶች ልብሶችና የመዋቢያ ቁሳቁሶች ላይ የሚስተዋለው የሦስቱ ቀለማት ኅብር ዋጋ የለሽ ሆኗል። በየአደባባዩና በየቤተ እምነቱ የምናያቸው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ጥብጣቦች ምንም ዋጋና ክብር የሌላቸው ተራ ጨርቆች ሆነዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስና የአትሌቲክስ ቡድኖች ማልያም ቢሆን ትርጉም አጥቷል። ጉዳት ሁለት።

ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች የክፍለ ጦሩን ዓርማ በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያትሙ ዘንድ ይፈቀድ ነበር። አሁን ሰንደቅ ዓላማው በአዋጅ አንድ ወጥ በመደረጉ ጦሩ ይህ ዕድል እንዳያገኘው ተደርጓል። ሌላው ቀርቶ የመቶ፣ የሃምሳና የአሥር ብር ኖቶች በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለሞች እንዲዋቡ የተደረጉት ሰንደቅ ዓላማውን መሠረት አድርገው በመሆኑ ይህም ትርጉም አልባ ሆኗል። ለማጠቃለል መንግሥት፣ መንግሥታዊ ሰነዶችን ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት ዓርማ የሚያስፈልገው እንደመሆኑ መጠን ይህን በሕገ መንግሥቱ መደንገጉ እምብዛም ለመቀበል አዳጋች አይሆንብኝም። ችግሩ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ዓርማው በግድ እንዲቀመጥ መደረጉ ነው። ሰንደቅ ዓላማ የገዢው ፓርቲ ወይም መንግሥት ሳይሆን የጠቅላላው ሕዝብ ሀብት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሰንደቅ ዓላማው፣ ሰንደቅ ዓላማውን ከሕዝብ የለያየው አዋጅ 654/2001 መሻሻል በተለይም አንቀጽ 16 መሰረዝ አለበት። የተወካዮች ምክር ቤትም በሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ላይ ለምን ተቃውሞ በዛ ማለቱን ትቶ ይህን አዋጅ መለስ ብሎ እንዲያየው ማሳሰብ እወዳለሁ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በአርባምንጭ ታስረዉ የነበረ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተፈረደባቸው

በ2006 ዓም በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ረብሻ አስነስታችሁዋላ በሚል ከታሰሩት መካከል 4 ተማሪዎች በ2 አመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ፍርድ ቤት ውሳኔ አስተላልፏል። ሁለቱ የ4ኛ 5ኛ አመት የህክምና ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ድግሞ የ3ኛ አመት የነርሲንግ ተማሪዎች ናቸው።በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የሚከተሉትን የአለባበስና የምግብ ስነስርአት መመሪያን ተግባራዊ ለማድረግ በዛሬው እለት በአዳማ ዩኒቨርስቲ እንቅስቃሴ መጀመሩ ታውቋል። መንግስት ያወጣውን ህግ ተግባራዊ ለማድረግ በሚንቀሳቀስበት ወቅት መጠነኛ የሆነ ግርግር በዩኒቨርስቲው በር ላይ ተፈጥሯል።

መንግስት በ2003 ባወጣው መመሪያ የእስልምና እምነት ተከታይ ሴትተማሪዎች "ሂጃብ" ማድረግ የሚችሉ ሲሆን "ኒቃብ" መልበስ ግን አይችሉም። መንግስት ለጸጥታና ደህንነት ሲባል የተወሰደ እርምጃ ነው ብሎአል። ሃይማኖታዊ በአላትና ዝግጅቶችን በትምህርት ተቋማት ማካሄድ፣ በቡድን ሰበካ ማካሄድ፣ በቡድን መዘመር፣ በቡድን መጸለይና በቡድን መስገድ እንዲሁም የሃይማኖት መቀስቀሻ የሆኑና ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችን በትምህርት ተቋማት ግቢ ማሰራጨትና በመቀስቀሻነት መጠቀም ተከልክሏል። በምግብ አዳራሽ መመገቢያ ሰአት በግል የህሊና ጸሎት ማድረግ የሚቻል ሲሆን በቡድን ወይም ከአንድ በላይ በመሆን መጸለይ አይቻልም።

## እንግሊዝ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎቿን ከየሐይማኖትና ከጎሳና የፖለቲካ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የእንግሊዝ መንግስት በኢትዮጵያውያን፤ በአለማቀፍ የሰብአዊ ሙብት ተሟጋች ድርጅቶችና የህግ አካላት እየደረሰበት ባለው ከፍተኛ ተቃውሞ ለጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ይሰጥ የነበረውን እርዳታ ለመሰረዝ እየተገደደ መሆኑን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን በቅርቡም ለጉጅሌዎቹ የማስተርስ ትምህርት ስልጠናና ለፖሊሲና ደህንነት አካላት ማጠናከሪያ በሚል ይሰጥ የነበረውን በድምሩ ከ 95 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ እርዳታ መሰረዙ አይዘነጋም።